# ምሥጢረ ጥምቀት

## የጥምቀት አፈጻጸም

ጥምቀት አጥመቀ (አጠመቀ) ካለው ግስ የወጣ ነው። ፍቺውም **በግብር** መንከር፣ መድፈቅ፣ መዝፈቅ ሲሆን **በተገብሮ** መነከር፣ መደፈቅ፣ መዘፈቅ፣ መላ አካልን ውኃ ውስጥ ማስገባት ማለት ነው።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የምታጠምቀው ከላይ እንደታተተው በትርጉሙ መሠረት ተጠማቂውን ውኃ ውስጥ በማጥለቅ ነው። ይህም ማለት ውኃው የተጠማቂውን መላ ሰውነት እስኪያለብስ ድረስ መላ አካሉን ውኃ ውስጥ በመድፈቅ ወይም ከራስ ጀምሮ በሰውነት ላይ በማፍሰስ ነው።

ሥርዓተ ጥምቀቱ በዘፈቀደ የሚከናወን ሳይሆን ትርጉምና ምሳሌ ባለው ሥርዓትን በጠበቀ መልኩ ነው። በቅድሚያ ለማጥመቂያ በተዘጋጀው ውኃ ላይ ካህኑ ጸሎተ ጥምቀት ያደርስበታል። ጸሎተ ጥምቀቱን ካህኑ ሲጸልይ እጁን በተጠማቂው ላይ ጭኖ ነው።

የተጠማቂውን የክርስትና ስም ሲሰይምም እጁን በትእምርተ መስቀል በተጠማቂው ላይ አኑሮ ‹‹**ይኩን ስምከ/ ስምኪ** (ወልደ ኢየሱስ፣ ወለተ ኢየሱስ ወዘተ)›› እያለ ስመ ጥምቀቱን ሦስት ጊዜ በመጥራት ነው።

በሚጠመቅበት ጊዜ ተጠማቂው ፊቱን ወደ ምዕራብ ይመልሳል። ወደ ምዕራብ የሚመልስበት ምክንያት አዳም ትእዛዘ እግዚአብሔርን ጥሶ ወደ ሲዖል መውረዱን ለማዘከር ነው። ሲኦል በምዕራብ ናትና። በመቀጠል ተጠማቂው በውኃው አንገር መቆም ይኖርበታል። ይኸውም የሚያመለክተው አዳም አባታችን የድኅነትን ተስፋ መስማቱን ለማዘከር ነው። ምክንያቱም ድኅነት በጥምቀት ነውና (ማር. 16÷16)።

ካህኑ ካጠመቀው በኋላ የተጠማቂውን እጁን ይዞ ወደ ምሥራቅ ፊቱን የሚመልስበት ምክንያት ጌታ በጥምቀት ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከሲዖል ወደ ገነት እንደመለሰን ለማስረዳት ነው። ምሥራቅ የገነት (ዘፍ.2÷8)፤ የእመቤታችን (ሕዝ.44÷1-9) ምሳሌ ጌታ የተሰቀለባት መድኀኒት

የተገኘባት ናትና፡፡ «እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፡፡» (ዮሐ.3÷5)፡፡

ካህኑ በተጠማቂው ፊት ላይ «ንሣዕ መንፈስ ቅዱስ - መንፈስ ቅዱስን ተቀበል›› እያለ እፍ ይልበታል፡፡ ቀጥሎ ቅብዐ ሜሮን ይቀባዋል፡፡ ካህኑ ሜሮን ሲቀባ የተጠማቂውን ሰውነት ክፍል ክፍሉን እየለየ በትእምርተ መስቀል ሠላሳ ስድስት ሕዋሳቱን ይቀባዋል፡፡ በመጽሐፈ ጥምቀት እንደተገለጠው ካህኑ ሴቷን ካደገች በኋላ አምና የምትጠመቀውን ካንገቷ በላይ ያሉትን አካላቷን ይቀባል፡፡ ካንገቷ በታች ያሉት አካላቷን ዲያቆናዊት ሴት የካህኑን እጅ ይዛ ትቀባታለች፡፡ በጸሎተ ቡራኬና አንብሮተ እድ በተጠማቂው ላይ ይጸልያል፡፡ ከዚህ በኋላ ለክርስትና አባቱ ሲሰጠው አዲስ ልብስ ያለብሰዋል፡፡ ይህም አበሳው እንደተወገደለት መታደስን እንዳገኘ ያሳያል (ዘካ.3÷1-5)፡፡

ጥምቀት በሚያጠልቅ ውኃ እንዲሆን የታዘዘበት ምክንያት የተጠማቂውን መላ አካል እንዲያጠልቀው ተብሎ ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን «ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን፡፡» (ሮሜ.6÷34)፡፡

በጥምቀት ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረን መቀበራችንን ሐዋርያው አስገንዝቦናል፡፡ መቃብር ደግሞ መላ ሰውነትን የሚውጥ (የሚያለብስ) እንደመሆኑ ከጌታ ጋር አብረን የመቀበራችንን ምሥጢር የሚገልጠው ጥምቀትም መላ አካላችንን ማለትም ከራስ ጠጉራችን እስከ እግር ጥፍራችን ድረስ የሚያጠልቅ (የሚያለብስ) ውኃ መሆን አለበት፡፡

በተጨማሪም በጥምቀት ከእግዚአብሔር በጸጋ የምንወለድ በመሆኑ መላ አካላችን ውኃ ውስጥ ጠልቆ መውጣት ይኖርበታል፡፡ የሥነ ፍጥረትን ሕግ ተከትለን ስንሄድ መወለድ ከተሰወረ፣ ከማይታይ ጨለማ መውጣት እንደሆነው ሁሉ ጥምቀትም (ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተጎናጽፈን ብርሃን ለብሰን ከእግዚአብሔር የምንወለድ በመሆኑ) የተጠማቂውን መላ አካል ውኃ ውስጥ ጠልቆ ማውጣት ይሆናል፡፡ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ፣ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ መወለዱን ለማረጋገጥ፡፡

ካህኑ ተጠማቂውን በውኃው ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ የሚያደርግበት ምክንያቱ ምሳሌ አለው፡፡ ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው መጥለቅ ወደ መቃብር የመውረድ ሲሆን መውጣት (ብቅ) ማለት ደግሞ

የትንሣኤ ምሳሌ ነው፡፡ ይህ ግብር ሦስት ጊዜ መፈጸሙ ደግሞ የሥላሴ ምሳሌ ሲሆን ግብሩ ደግሞ አንድ ዓይነት መሆኑ የአንድነት ምሳሌ ነው፡፡ እንዲሁም በውኃው ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ማለቱ ክርስቶስ በከርሠ መቃብር 3 መዓልት 3 ሌሊት አድሮ የመነሣቱ ምሳሌ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስም ጥምቀት ውኃ ውስጥ መላ አካልን በማጥለቅ መከናወን እንዳለበት ያስረዳል፡፡ ለዚህም እንደምሳሌነት አድርገን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀትና ቅዱስ ፊልጶስ ያጠመቀውን የኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬን ጃንደረባ ልንወስድ እንችላለን፡፡ ጌታ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ መላ አካሉን ውኃ ውስጥ ጠልቆ በመውጣት እንደ ነበር ማስተዋል ይቻላል፡፡ ይህንንም ወንጌላዊው ቅ/ማቴዎስ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡፡ «ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ» (ማቴ.3÷16፤ ማር.1÷10)፡፡

ሐዋርያው ፊልጶስም ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ባጠመቀበት ጊዜ ወደ ወንዝ አውርዶ መላ አካሉን ውኃ ውስጥ አጥልቆ እንዳጠመቀው «ከውኃ ከወጣ በኋላ» የሚለው አነጋገር ያስገነዝበናል (የሐዋ.8÷38-39)፡፡

የጥምቀት ምሥጢራዊ ትርጉሙ ከክርስቶስ ጋር አብሮ መቀበር ማለት መሆኑን ከላይ ገልጸናል፡፡ መቃብር ደግሞ ሙሉ አካልን የሚውጥ እንጂ ከፊሉን ውጦ ሌላውን የሚያስቀር አይደለም፡፡ ሁሉም አካል በመሬት ውስጥ ይዋጣል፡፡ ከጌታችን ጋር አብረን መቀበራችንን ለማስመስከር ስንጠመቅም መላ አካላችን ውኃ ውስጥ ሊጠልቅ እንደሚገባውም ከላይ ተገልጿል፡፡ ለዚህ ማጠናከሪያ የሚሆኑ ማስረጃዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ መጥቀስ ቢቻልም «ለጠቢብ ሰው አንዲት ቃል ትበቃለች» ስለተባለ፣ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቈላስይስ ሰዎች በላከው መልእክት ላይ ጥምቀትን አስመልክቶ የተናገረውን በመጥቀስ ይህን ንዑስ ርእሳችንን እናጠቃልላለን፡፡ «**በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ለይቶ በአስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ**» (ቈላ. 2÷12)፡፡ በተጨማሪም በጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የማጥመቂያ ገንዳዎች መገኘታቸው የመጠመቂያ ውኃ ሰውነትን ለማጥለቅ እንዲችል ሆኖ መዘጋጀት እንዳለበት ያስረዳል፡፡